abookmwdwirchitotpress.com

4ኛ ዓመት ቁጥር 5
4th Year No. 5

ሐረር ጥቅምት 20/1991
Harar oct. 30/1998

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| ያንዱ ዋጋ 1.00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 11/1991
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለ1991 የበጀት ዓመት ሥራዎች የታወጀ
የበጀት አዋጅ ቁጥር 11/1991------------------------------ ገጽ 71

## አዋጅ ቁጥር 11/1991 ዓ.ም ለሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በ1991 በጀት የሚሰሩ ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ

በ1991 የበጀት ዓመት በክልሉ ውስጥ የሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት በበጀት አመቱ መጀመሪያ ላይ አጽድቆ ሥራ ላይ የማዋል አስፈላጊ በመሆኑ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 52 በንዑስ አንቀጽ 2/ሠ/ መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ የ1991 በጀት ዓመት በጀት አጠቃሎ ማጽደቅና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል 1

### ጠቅላላ

**አንቀጽ 1** ይህ አዋጅ የ1991 በጀት ዓመት በጀት አዋጅ ቁጥር 11/1991 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

abookmwdwirchitordpress.com



3. የበጀት ዝውውር ሥልጣን ለሚከተሉት አካላት ተሰጥቶአል

ሀ/ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

1. በጀት ተፈቅዶለት በመከናወኛ ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ የካፒታል በጀት

2. መደበኛ በጀት ከተፈቀደለት አርዕስት /ንዑስ አርዕስት በበጀት ዓመቱ መደበኛ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት/ ንዑስ አርዕስት

3. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደለት ወደ ካፒታል በጀት፤

4. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ

ለ/ የፋይናንስ ቢሮ

1. ከላይ በአንቀጽ 6ሀ ከ1-4 ከተጠቀሰው በስተቀር ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሲጠየቁ በአንዱ መደበኛ በጀት አርዕስት ውስጥ ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላው ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ

2. ጉዳዩ የሚመለከተው የክልሉ መንግሥት አካልና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲስማሙበት በአንድ የክልሉ መንግሥት አካል ሥር ለአንድ አርዕስት፣ ንዑስ አርዕስት ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደን የካፒታል በጀት ወደ ሌላ አርዕስት ንዑስ አርዕስት፣ ፕሮጀክት በየሂሳብ መደቡ

3. በሥራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ በክልሉ በመደበኛ በጀት ውስጥ ለመጠባበቂያ በተያዘው ወደ ሌሎች ወጪዎች፤

4. በሥራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ በክልሉ ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለውን ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ወጪዎች

ነሐሴ 17 ቀን 1990 ዓ.ም

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መንግሥት

ፕሬዝዳንት

abookmedwin.wordpress.com



# ክልላዊ ወጪ አሸፋፈን

## I. ወጪ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ | መደበኛ ወጪ | ብር | ድምር |
| | ክልል ም/ቤት | 3,198,900 | |
| | ኦዲት ጽ/ቤት | 418,600 | |
| | የኢኮኖሚ ዘርፍ | 5,153,800 | |
| | የፍትህና ፀጥታ ዘርፍ | 6,651,200 | |
| | የከተማና አስተዳደር ዘርፍ | 2,417,800 | |
| | የማህበራዊ ዘርፍ | 24,014,000 | |
| | መጠባበቂያ | 2,000,000 | |
| | የመደበኛ ወጪ ድምር | | **43,854,300** |
| | II የወጪ አሸፋፈን | | |
| ለ | የካፒታል ወጪ | | ድምር |
| | የኢኮኖሚ ልማት | 30,544,800 | |
| | ማህበራዊ ልማት | 10,303,745 | |
| | ጠቅላላ አገልግሎት | 10,949,655 | |
| | የካፒታል ወጪ ድምር | | 51,798,200 |
| | የወጪ ጠቅላላ ድምር | | 95,652,500 |
| | ሀ. የሀገር ውስጥ ገቢ | | ድምር |
| | የታክስ ገቢ | 6,535,600 | |
| | ታክስ ያልሆነ ገቢ | 2,464,400 | |
| | የአገር ውስጥ ገቢ ድምር | 9,000,000 | |
| | በጀት መርጃ | 80,311,100 | |
| | ጠቅላላ ገቢ | | **89,311,100** |
| ለ. | የውጭ ዕርዳታ | | |
| | የጥሬ ገንዘብ ዕርዳታ /ካውንተር ፓርት ፈንድ/ | 881,700 | 881,700 |
| ሐ. | ብድር | | ድምር |
| | የውጭ አገር ብድር | 5,459,700 | 5,459,700 |
| | የገቢ የዕርዳታና የብድር ጠ.ድምር | | **95,652,500** |